*ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ህያው ሆኖአል ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም*
*ሉቃስ ምዕ15ቁ24*

## "የጠፋው ልጅ"

ወጥተህ ወርደህ ከማትረፍ
ወጥተህ ወርደህ አጥፍተህ
የዓለም ክፋቷ አይሎብህ
የአባትህን ቃል ጥለህ
ምርቃቱን ባርኮቱን ንቀህ
ማደርያህን ተፀይፈህ
ማረፊያ ቦታህን ትተህ
የከበረውን ችላ ብለህ
ያልከበረውን ለማንሳት
እስኪ ምን አመጣው
ገንዘብን ሰብስቦ መጥፋት
ስትሯሯጥ ልክፍት ይዞህ
ዓለም ምን ጠቀመችህ
ምንስ አጥተህ ምን ሰጠችህ።
ሰውነትህን አርክሳ
በበደል በኃጢአት ዳብሳ
በሰላ ጥረቧ ይዛ ነክሳ
መፈናፈኛ አሳጥታ
በክፋት ነድፋ
በመጠጥ ስካር ብዛት
መልሳ እራስህ ላይ ስታስተፋ
በያር በዝሙት ለክፋ
በረሀብ አለንጋ ጠብሳ አመንምና
መጎናፀፊያህን አስወልቃ
መሬት አስጥላ አስረግጣ
ድሪቶን አስለብሳ
በመጥፎ ጠረን ወርሳ
አንገትህን አስደፍታ
እንደዶሮ መሬት አስጭራ
አስጎንብሳ ከእርያ ጋራ ስታስበላ
በእሾህ አሜኬላ ሰውነትህን ወግታ
ደምህን ስታዘራ የድካም ላብ አስልባ
መላ አሳጥታ ግራ ስታጋባ
ገደል ለገደል ዱር ለዱር ስታዘልልህ
ድርሻህን አስረክበኻት

አብረውህ የበሉት
የወረት ልጆቿ ሳይቀሩ
መጣብን እያሉ በድንጋይ እየወገሩ
ከምድረ- ገፅ እንዲያጠፉህ
የማትሳሳ ጨካኝ አውሬ
መሆኗን ስታሳይህ
አሳልፋ ሰጥታ ስታስነውርህ
ያለህን ከእጅህ ወስዳ
በሰደድ እሳት ማግዳ
በእምቢታ አስገድዳ
የቀረችህን ያቺን ተስፋ
ለማምከን ስትነሳ
ያኔ ነበር !ያኔ ነበር!
የአባትህ ፀሎት የረዳህ
የልጅነት መንፈስ የጠራህ
በህሊናህ ሁሉም ተቀርፆ
ብርሃን ሆኖ ተገልፆ
አሰተዳደግህን እንደመስተዋት ሲያሳይህ
ወለል ብሎ ምስጢሩ
መልካም አንደበቱ ሰናይ ምክሩ
የአባትህ ቤት መዓዛ ማማሩ
ያ ለምለም ስፍራ ውበቱ
የመንፈስ ብርታት ፅናቱ
ራስን ፈልጎ የማግኘቱ
የሃይማኖት የእምነት ብድራቱ
የስነ-ምግባሩ ብልፅግና
የዕውቀት ሞገሱ ፋና
ደዌ የሌለበት ፍፁም ጤና
ደጅ የጠናህበት ያ የጥንቱ
ከአባትህ ጋር ያስተሳሰረህ መቀነቱ
ጨርሶ ሳይፈታ ጠብቆ ኖሮ
ድል ነሳልህ ይኸው ዲያብሎስን አባሮ
እመቀመቅ ጥሎልህ አሽቀንጥሮ
እያሳየህ ሲጫወቱ ቤቱን ሞልተው
አገልጋዮች ሎሌዎቹ
አዛውንት ባልቴቶቹ
ሕፃናት አዋቂዎቹ
ሳቅ በሳቅ ሆኖ ዙሪያው
እየበሉ እየጠጡ
ውሻ እንኳን ሳይቀር ጠግቦ

የሚበላው ፊቱ ቀርቦ
አየኸው! ፍሪፍሪውን እንኳን ሲያስመኝህ
የአባትህን ቤት ሲያስናፍቅህ
ይኼ እኮ ታዲያ መመለስ ነው
ንስሐን ነው የሚያዘክረው
የመዳንህ ቀን ቀርቦ
በምስራቹ ሰው ተሰብስቦ
አየኸው ዓለምን ተቀብለህ
አውጥታ ስትጥልህ
መቼ ጨከነ አባትህ
ወጣ እንጂ ሮጦ
ልጄ ብሎ ሊቀበልህ
ዕንቢልታውን እያስነፋ
ነጋሪቱን እያስጎሰመ
ዝማሬው ዕልልታው ቀልጦ
እያስተጋባ ሰማይ ምድሩ
አቤት!...አቤት! ላንተ ያቺ ቀን
ምን ብሩክ ቀን ናት?
እንደምን ያለችስ ዓመት ናት?
ከቀንም ቀን ተመርጣ
ከዓመትም ዓመት ተለይታ
ስትሰጥህ ለድህነት
አባትህ ራርቶ ጉንጭህን እየሳመ
የጠፋው ልጄ ተገኝቶ ተመለሰ
በቤቴ ዳግም ሰላም ነገሠ
ደስ ብሎኛል ደስ ይበላችሁ
ዕልል በሉ እዚህ ያላችሁ
የክብር ልበስ አልብሱት
መጎናፀፊያውን ደርቡለት
መጫሚያውን አድርጉለት
ከፍ ባለ ቦታም አስቀምጡት
እያለ ሐሴት ሲያደርግ
እውነትም ያሰኛል ከአባትም አባት
ከጌታም ጌታ
የልጁ መጥፋት ግድ ብሎት ያሳሰበው
ሲገኝለት ይሁን ያለው
ርህሩህ ጌታ እሱ እኮ ነው
ታማኝ አባት ይቅር ባይ ነው።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ (ለንደን፡ነሐሴ 2003 ዓ/ም)